በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን።

# ንስሐና ቅዱስ ቁርባን

መምህር፡- ቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን
አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
ጥቅምት ፳፫ ቀን ፳፻፬
ዓ.ም.

# ምስጢረ ንስሐ

- ንሥሐ ከሰባቱ ምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አንዱ ነው::

- በቤተ ክርስቲያን ትምህርት:- ሰው ከተሳሳተ ኹለት ነገሮች ያስፈልጉታል::
  - ሀ. ንስሐ:- ንስሐ ማለት «ነስሐ» ተጸጸተ፣ ተቆረቆረ፣ ከሚለው የግዕዝ ግስ የወጣ ነው:: በሠሩት የማይገባ ሥራ ወይም ኃጢአት ማዘን፣ ምነው ባልሠራኹት ምነው ባላደረግሁት፣ ምን ቀን ጣለኝ፣ ብሎ መቆጨት ነው:: የሚጸጸት ፍጡር ሰው ብቻ ነው ሌሎች ፍጥረታት የመጸጸት ስሜት የላቸውም::

  - ለ. ኑዛዜ:- /ኃጢአታቸውን የሚናዘዙ እግዚአብሔርን ያስደስታሉ/ ሉቃ 15፣7-10:: ኑዛዜ ማለት ደግሞ አንድ ሥራ ከሰራ በኋላ ያንኑ ሳይደብቅ ሳይቀንስ ጨርሶ መናገር ማለት ነው:: ንስሐ ለማግኘትም የጸጸት መግለጫ ይኾናል ኑዛዜም እንደዚኹ ነው ኃጢአትን መናገር ብቻ ሳይኾን ማንኛውም ሰው ሊሞት ሲል ኃብቴን ንብረቴን ለዕገሌ ሰጥቻለሁ ብሎ በቄስ ፊት የሚናገረው የመጨረሻ ንግግር ኑዛዜ ይባላል::

- በቄሱ አድሮ ኑዛዜውን የሚሰማውና ሥርየትም የሚሰጠው መንፈስቅዱስ ነው::

- በሐዋርያት ጊዜ ከዚያም በኋላ ለረጅም ጊዜ ኑዛዜ በአደባባይ በሕዝብ ፊት ነበር:: ለምሣሌ ቅዱስ ጳውሎስ በኤፌሶን አደባባይ የሕዝቡን ኑዛዜ ይቀበል ነበር:: “አምነውም ከነበሩት እጅግ ሰዎች ያደረጉትን እየተናዘዙና እየተናገሩ ይመጡ ነበር::” የሐዋ. ሥራ 19*18:: 2ኛ ቆሮ 7*11 :: ያዕቆብ 5*16::

# ምስጢረ ንስሐ የቀጠለ...

- የኃጢአትን ሥርየት በምሥጢር የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ ቢኾንም አገለግሎቱን የሚፈጽሙ ካህናት ናቸው:: ይህም ለሐዋርያት ጌታ በማስተማር ዘመኑ #በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይኾናል፤ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይኾናል; በማለት በሰጠው ሥልጣን የሚፈጸም ነው:: ማቴ 16*19:: ዮሐ 20*21:: የሐዋ. 5*1-11:: 8*20-22:: 13*8-12::

- የምሥጢረ ንሥሐ አፈጻጸም ተነሳሒው በፈጸመው የማይገባ ሥራ ተጸጽቶ ለወደፊቱ ወደዚህ ክፉ ሥራ አልመለስም ብሎ ወስኖ በፍጹም እምነትና በክርስቲያናዊ ተስፋ ተሞልቶ ማለት የተስፋ ስንቁን ቋጥሮ ወደ ቄሱ ይገሰግሳል የስራውንም ጥፋት አንድ ሳይቀር በቄሱ ፊት ይናዘዛል:: ቄሱም በተሰጠው ሥልጣን በትምህርት በቀኖና ሥርየተ ኃጢአትን ይሰጠዋል ቀኖናውን ከፈጸመ በኋላ ሥርየተ ኃጢአትን ያገኛል ወደ ቀድሞው ክርስቲያናዊ ክብሩ ይመለሳል::

- "ኃጢአታቸውን ይቅር ያላችኂቸው ሁሉ ይቀርላቸዋል፤ የያዛችሁባቸው ተይዞባቸዋል አላቸው::" ዮሐ_:::

- "እውነት እላችኂለሁ፥ በምድር የምታስሩት ሁሉ በሰማይ የታሰረ ይሆናል፥ በምድርም የምትፈቱት ሁሉ በሰማይ የተፈታ ይሆናል::" ማቴ_:::

# ምስጢረ ንስሐ የቀጠለ...

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ትውፊት ማንኛውም ምዕመን ከአጥቢያው ቄሶች ውስጥ መምህረ ንሥሐ መርጦ ይይዛል፡፡

- ይህም የነፍስ አባት ይባላል፡፡ ቄሱ ለምዕመኑ የነፍስ አባት፣ የንስሐ አባት፣ መምህረ ንስሐ ይባላል፡፡ ምዕመኑም ለቄሱ  የነፍስ ልጅ፣ የንስሐ ልጅ ይባላል፡፡

- ቄሱ በመከራም ኾነ በደስታ ጊዜ ከነፍስ ልጆቹ አይለይም፡፡ ምዕመናኑም ጥፋታቸውን የሚናዘዙት በቤተ ክርስቲያናችን ትውፊት መሠረት በምሥጢር በግል ነው፡፡ አሁን ግን ከጊዜ ብዛትና  ከትምህርትም ማነስ የተነሳ አንዳንድ ምዕመናን ሲወልዱ ለማጥመቅ፣ ሲሞቱ ለፍታት  ካልኾነ በቀር ኃጢአትን በየጊዜው ለመናዘዝና ሥርየተ ኃጢአትን ለማግኘት  ወደ ቄሱ የሚሔድ የለም፡፡

- መስቀል ተሳልሞ «ይፍቱኝ» ማለት ሞልቷል ታዲያ ምዕመኑ ከኃጢአት ማሠሪያ የሚፈታው ኃጢአቱን ተናግሮ ቄሱ በቤተ ክርስቲያን የሚሰጠውን ቀኖና ሲፈጽም ነው፡፡ ከዚህም ጋር የኑዛዜ ጉዳይ በቤተ ክርስቲያናችን እየተረሳ ስለሔደ ብዙ ሰዎች ኑዛዜው በዓመት አንድ ቀን «የስቅለተ ዓርብ» የሚጠበጠቡትንና የሚናዘዙትን ይመስላቸዋል፡፡

- አማንያን ከልጅነት በኋላ በኃጢአት ከሚያገኘን ሞት የምንላቀቀው በንስሐ ስለሆነ ዘወትር በደላችንን እያሰብን ራሳችንን ማስመርመር አስፈላጊያችን ነው፡፡ ጌታችን "ነገር ግን ንስሐ ባትገቡ ሁላችሁ እንዲሁ ትጠፋላችሁ፡፡" ብሎናልና፡፡ <u>*ሉቃ 13፡3፡፡*</u>

# ምስጢረ ንስሐ በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት

- በምሥራቅ መለካውያን ሥርዓት የምዕመናንን ኑዛዜ ለመስማት የሚችሉት ከኤጲስ ቆጶሳት ልዩ ፈቃድ ያላቸው ቄሶች ብቻ ናቸው፤ ምእመናኑም የወደዱትን ቄስ መርጠው የነፍስ አባት ለማድረግ አይችሉም፡፡

- ምሥጢረ ንሰሐ በሮማ ካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንም አለ፡፡ ኑዛዜውም በየጊዜው ነው፡፡ ነገር ግን ቀኖና አሰጣጡ ከኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተለየ ነው፡፡ ተናዛዡ ሀብታም ከኾነ ቀኖናውን በገንዘብ ይዋጀዋል፡፡

- በፕሮቴስታንት ዓለም ደግሞ የቀሳውስትን የማሠርና የመፍታት ሥልጣን ስለማይቀበሉ የንሰሐንና የኑዛዜን ምሥጢርነትም አያውቁም፤ ተሳስተናል ወይም እንሳሳታለን ማለት በእነሱ ዘንድ ሩቅ ነው፡፡

- በኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን «ፍትሐ መንፈሳዊ» እና «ፈውስ መንፈሳዊ» የተባሉ የስሕተቱን ጠባይና ቀኖናውንም አቀናብረው የሚናገሩ መጻሕፍት አሉ፡፡

# ምስጢረ ቁርባን

- ቁርባን የሱርስት ቃል ነው መባዕ፣ ስጦታ፣ አምኃ ማለት ነው። ሥጋውና ደሙ የተሰጠን በነጻ ያለዋጋ ሳይገባን በችሮታ ነውና። ቁርባን ይባላል። ዮሐ 6፥ 32-63።

- ሥጋውና ደሙ የሚዘጋጀው ከስንዴና ከወይን ነው።

- ምስጢረ ቁርባንን የመሠረተው ራሱ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። «ከሰማይ የወረደ ኅብሥት እኔ ነኝ ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው» እያለ ያስተማረውን ተማሪዎቹ በምር እንዲረዱት የጸሎተ ሐሙስ ዕለት ማታ ለበረከት ከመጣለት ኅብስት ያላረረውን ያልጠቆረውን ነቅዕ ነጭ የሌለውን አንሥቶ ባርኮ ፈትቶ አቀጣጥኖ "ነገ ስለ እናንተ በመልዕልተ መስቀል የሚቆረሰው ሥጋዬ ይህ ነው እንኩ ብሉ ብሎ ሰጣቸው።" ወይኑንም እንደዚሁ ባርኮ "ነገ ስለናንተ በመልዕልተ መስቀል የሚፈሰው ደሜ ይህ ነው እንኩ ጠጡ ብሎ ሰጣቸው።" ዮሐ 6፥32-63፡
- ይህን ከሰጣቸው በኋላ ሞቱንና ትንሣኤውን እያነሱ እያስታወሱ ኹል ጊዜ ይህን እንዲያደርጉ አዟቸዋል። ማቴ. 26 ፥ 26-28። ማር. 14 ፥ 22-24። ሉቃ 22 ፥ 19-20

- የክርስቶስ መሥዋዕትነት በብሉይ ኪዳን ለአያሌ ዓመታት በትንቢት፣ በምሳሌ ሲነገር የኖረ ነው። ዘፀ 12 ፥ 13 ኢሳ.53 ፥ 7። ኤር.11 ፥ 19።

# ምስጢረ ቁርባን ...

- በኦሪት ዘፍጥረት እንደተገለጠው መልከ ጼዴቅ ለአብርሃም መስተንግዶ ያቀረበው ኅብስትና ወይን የክርስቶስ ሥጋና ደም ምሳሌ ኹኗል:: ዘፍጥ 14 ፥ 18-19: 1ኛ ጴጥ 1 ፥ 19:: ዮሐ.1 ፥ 29-36:: ራዕይ 5 ፥ 6-12

- እሥራኤል በምድረ በዳ በተአምራት ከሰማይ እየወረደላቸው አርባ ዓመት ሙሉ የተመገቡት በተአምራት በመገኘቱ ለሥጋውና ለደሙ ምሣሌ ኹኗል:: ዮሐ 6 ፥ 49::

- ሐዋርያት በማስተማር ዘመናቸው ኹሉ ምሥጢረ ቁርባንን ይፈጽሙ ነበር:: ነገር ግን እንደዚህ እንደ አኹኑ ቤተ ክርስቲያን ነጻነቷን አግኝታ እንደምታደርገው በይፋ ሳይኾን በምዕመናን ቤት ነበር::

- ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ እንደገለጠው ኹል ጊዜ ከማስተማርና ከጸሎት ጋር ምሥጢረ ቁርባንም ነበር:: የሐዋ. ሥራ 20 ፥ 27:: 2 ፥ 42::

- ተማሪው ሉቃስ በሐዋርያት ሥራ «ፈትቶ ኅብሥት» እያለ በተራ ቃል የገለጠውን መምህሩ ቅዱስ ጳውሎስ «የጌታ ማዕድ፣ የጌታ ጽዋ» ብሎታል:: 1ኛ ቆሮ. 10 ፥ 21:: እንዲያውም የጌታ ሥጋና ደም እያለ ገልጦ ያስተምር ነበር:: 1ኛ ቆሮ 11 ፥27::

# ምስጢረ ቁርባን …

- በዓመተ ሰማዕታት የነበሩ ክርስቲያኖችም ማለት እስከ አራተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ የነበሩት ክርስቲያኖች በየተሰደዱበት ቦታ በዋሻ፣ በፍርክታ ውስጥ ምሥጢረ ቁርባንን ይፈጽሙ ነበር።
- ከዚህም የተነሳ ባላመኑ አረማውያን ዘንድ ክርስቲያኖች ሰው ይበላሉ እየተባሉ ይወነጀሉ እንደነበር በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተመዝግቧል። ምንጊዜም ቢኾን ንዜኑ ሞተከ ወትንሣኤከ፡- «ሞትህንና ትንሣኤህን አንረሳም ሕይወታችን ነውና ደግሞም ምጽአትህንም በናፍቆት እንጠባበቃለን›› እያሉ ክርስቲያኖች የክርስቶስን መከራ በቅዳሴ ጊዜ ይዘምሩታል። ከሕይወታቸውም ፍጻሜ በኋላ ስለሚወርሱት ሕይወት ያላቸውን ተስፋና ተስፋውንም በናፍቆት የሚጠባበቁ መኾናቸውን ይገልጣሉ።
- ምስጢረ ቁርባን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የጌታን፣ የሐዋርያትን ከዚያም የቤተ ክርስቲያን አባቶች ያቀዩትን ሥርዓት መሠረት በማድረግ ይፈጸማል።
- መሥዋዕቱ የሚዘጋጀው በቤተ ክርስቲያኑ ቅጽር ውስጥ በስተ ምሥራቅ በኩል በሚገኘው ቤት ነው። ይህ ቤት «ቤተ ልሔም» ይባላል። ክርስቶስ በተወለደባት ከተማ በቤተ ልሔም የተሰየመ ነው። የክርስቶስ የማዳን ሥራው ከቤተልሔም እስከ ቀራንዮ ነው። -
- ቤተ ክርስቲያን ቀራንዮ ናት። መሥዋዕቱን የሚሰሩት ዲያቆናት ናቸው። በቤተልሔም መሥዋዕቱ ሲዘጋጅ ቄሱ በቤተ መቅደስ የመግቢያ ጸሎት ሲያደርግ ይቆያል። በቤተ መቅደስ ባሉት በንዋያተ ቅዱሳት ላይም ለእያንዳንዳቸው የታዘዘውን ቡራኬና ጸሎት ያደርሳል። ልብሰ ተክህኖውን ከመልበሱ በፊት በክንዱ ይዞ ይጸልያል ጸሎቱን ሲጨርስ ኤጲስ ቆጶሱ ያለዚያም በእድሜ የሚበልጠው በሹመት የሚቀድመው ቄስ ባርኮለት ኹሉም ካልተገኙ ራሱ ባርኮ ይለብሳል።

# ምስጢረ ቁርባን …

- ከዚህ በማያያዝ በንዋያቱ ላይ በየተራ የቡራኬ ጸሎት ይጸልያል በቤተ መቅደስ የሚገኙ ንዋያተ ከታቦቱ ሌላ የሚከተሉት ናቸው፡፡
  - ሀ. መሶበ ወርቅ፡- መሥዋዕቱ ከቤተልሔም የሚመጣበት ነው፣
  - ለ. ጽዋ፡- የደሙ መያዣ ነው፣
  - ሐ. ጻሕል፡- የሥጋው መያዣ፣
  - መ. እውድ፡- ምዕመናን ለማቁረብ ሥጋውን የሚይዙበት ፣
  - ሠ. ዕርፈ መስቀል፡- ደሙን የሚያቀብሉበት፣
  - ረ. ጽንሐሕ፡- ማጠኛው ሻኩራው
  - ሰ. ሙዳይ፡- የዕጣን መያዣ፣
  - ሸ. ማኅፈድ፡- ሥጋው በጻሕል ላይ የሚሸፈንበት፡፡

- እነዚህ ንዋያት በየተራ ይባረካሉ፡፡ በመጀመሪያም ለቤተ መቅደስ አገልግሎት የሚውሉት ሜሮን ተቀብተው ተባርከው ነው፡፡ በቅዳሴም ጊዜ በየአንዳንዳቸው የቡራኬ ጸሎት አላቸው፡፡

- የቤተ ልሔሙ ዝግጅት ሲያበቃ ቅዳሴውን የሚሳተፉት ዲያቆኖቹም ቄሶቹም እያስባረኩ ልብሰ ተክህኖአቸውን ይለብሳሉ በፊቱም ተንበርክከው ጸሎት ይቀበላሉ፤ ከዚህ በኋላ አንዱ ዲያቆን መሶበ ወርቁን ግምጃ አልብሶ በራሱ ተሸክሞ ንፍቁ ቄስ ሻኩራውን ይዞ ከኋላ እያጠነ መሥዋዕቱን ለማምጣት ወደ ቤተ ልሔም ይወርዳሉ፡፡ ቅዳሴ መጀመሩን የሚያውጅ ደወልም ይደውላል፡፡ ስለ ጸሎተ ቅዳሴ ተራ በመጽሐፈ ቅዳሴው ተጽፏል፡፡

- በቅዳሴ ጊዜ የሚነበቡ መጽሐፍት የሚከተሉት ናቸው፡፡
  - ሀ. ከጳውሎስ መልዕክታት፡- ሠራኢው ዲያቆን፣
  - ለ. ከሰባቱ መልእክታት፡- ንፍቁ ዲያቆን፣
  - ሐ. ከግብረ ሐዋርያት ንፍቁ ቄስ፣
  - መ. ምስባክ ከዳዊት መዝሙር፡- ሠራኢ ዲያቆን፣
  - ሠ. ከወንጌላት፣ ሠራኢው ቄስ

# ምስጢረ ቁርባን …

- «ጳጕ ንዑሰ ክርስቲያን» የሚባለውና ደወል የሚመታው ወንጌል ከተነበበ በኋላ ነው፡፡ የክርስትናን ትምህርት በመማር ላይ ያሉ ንዑሰ ክርስቲያን ወንጌል እስኪነበብ ድረስ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎቱን ይከታተላሉ፡፡ ከወንጌል በኋላ ግን ይወጡ ነበር፤ አኹን ግን ንዑሰ ክርስቲያን ቢኖሩም ባይኖሩም ዲያቆኑ «ጳጕ ንኡሰ ክርስቲያን» ብሎ ቃጭሉንም ደወሉንም ያስተጋባዋል፡፡ እስከዚህ ያለው የቅዳሴ ክፍል የሥርዓትና የትምህርት ክፍል ነው፡፡ ከዚህ በኋላ ጸዋትው አልቆ ፍሬ ቅዳሴ ይጀመራል ቄሱ «ሀበነ» ሲል መ ሥዋዕቱ ይለወጣል፡፡

- «ይወርድ መንፈስ ቅዱስ በላእለ ኅብስቱ ወወይኑ፣ ሶበ ይብል ካህን ፀጋ መንፈስ ቅዱስ ፈኑ» ብለው፤ … ድርገት ከመውረዳቸው በፊት አርባ አንድ ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ተብሎ፤ በውጭ ሃይማኖት አበው ይነበባል፡፡ በውስጥም ቄሱ ስለ ሥጋውና ደሙ ሦስት ጊዜ የምስክርነት ቃሉን ይሰጣል፡፡

1. በመጀመሪያ የምስክርነት ቃሉን ይህን ሥጋና ደም የእግዚአብሔር ልጅ ቅድስት ንጽሕት ከምትኾን ከእመቤታችን ድንግል ማርያም የነሣው መኾኑን አምናለኹ፡፡ ያለ መቀላቀል፣ ያለ መለየት ያለ መለወጥ አንድ አካል አንድ ባሕርይ የኾነ በጵናጠሱ በጲላጦስ ፊት እውነትን የመሰከረ፣

2. መለኮት ከትስብእት አለመለየቱን አምናለኹ አንድ ሰዓትም በኾን ለዐይን ጥቅሻ ያህልም እንኳ አምነን ለምንቀበለው ኹሉ ለሕይወትና ለመድኃኒት ለኃጢያትም ሥርየት ተሰጠን እንጅኖ

3. ከሰማያዊ ቸር አባቱና ከሕይወት ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ክብርና ምስጋና የሚገባው የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱሰ ክርስቶስ ሥጋውና ደሙ ይህ መኾኑን አምናለኹ ብሎ ይመሰክራል፡፡

# ምስጢረ ቁርባን …

- ይህ የምስክርነት ቃሉ፡- ተቀላቀለ፣ ተጣፋ የሚሉ እነአውጣኪን ከተዋሕዶ በኋላ አንድ አካል አንድ ባሕርይ አልኾነም የሚሉ መለካውያንን፣ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ያሳነሱትን እነ አርዮስን ያወግዛል።

- ከዚህ በኋላ የንስሐ ጸሎት ጸልዮ ይቆርባል። አብረውት የቀደሱትንም ያቆርባቸዋል። ድርገት ወርደው ምዕመናንን በሚያቆርቡበት ጊዜ ቄሱ ስጋውን፣ ዲያቆኑ ደሙን ያቀብላል።

- በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ቅዳሴ ለመቀደስ አምስት ልዑካን ያስፈልጋሉ፤ ሦስት ዲያቆናትና ኹለት ቄሶችን እነሱም፡- አንድ ሠራኢ ቄስኖ አንድ ንፍቅ ቄስ፣ አንድ ሠራኢ ዲያቆን፣ አንድ ንፍቅ ዲያቆን፣ አንድ አብ ናቸው። በገዳማትና በታላላቅ አድባራት ግን ሰባት ልዑካን ካልተሟሉ አይቀደስም።

- የቅዳሴው ሰዓት በጾም ወራተ በዘጠኝ ሰዓት ነው። በበዓለ ሃምሳና ቅዳሜ፡- በሠለስት፣ እሑድ በነግህ፣ በትንሣኤ በልደትና በጥምቀት ግን በመንፈቀ ሌሊት ይቀደሳል። ለሕዝብ አገልግሎት ተብሎ ነው እንጅ በታላላቅ ቦታዎች ከትንሣኤ፣ ከበአለ ሃምሳ፣ ከእሑድ፣ ቅዳሜ፣ ከልደትና ከጥምቀት በቀር ምንጊዜም ቅዳሴ በዘጠኝ ሰዓት ነው።

# ምስጢረ ቁርባን ...

- በመሠረቱ ቁርባን መቀበል ማለት የክርስቶስን አማናዊ ሥጋ አማናዊ ደም መቀበል ማለት ነው የምንቀበለው የክርስቶስ ሥጋና ደም ነፍስ የተለየው መለኮት የተዋሐደው ነው።

- የጌታም ቅድስት ነፍሱ ከቅድስት ሥጋው የተለየችው ወንጌላውያን እንደመሰከሩለት በዘጠኝ ሰዓት ነው። ማቴ. 27፥ 46-50። ማር. 15 ፥ 34-37። ሉቃ 23 ፥ 44-6 የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በዘጠኝ ሰዓት የምትቀድሰው ጌታ ለኛ ብሎ የሞተበትን ሰዓት ለማስታወስ ነው። «ይህን በምታደርጉበት ጊዜ የሞቴን መታሰቢያ ታደርጋላችሁ» ብሏልና። በተወሰኑ ዕለታት በሠለስት በነግህና በመንፈቀ ሌሊት የምንቀድሰውና ድርጊቶቹ የተፈጸሙባቸውን ሰዓቶች ለማስታወስ ነው።

- በሞት አፋፍ ላይ ያለ ሕመምተኛ ቀድሳችሁ አቁርቡኝ ቢል በማናቸውም ሰዓት ቀድሰው ያቆርቡታል። ቀዳሾቹ ግን ዘጠኝ ሰዓት እስኪኾን ድረስ በመቅደስ ውስጥ ቆይተው በዘጠኝ ሰዓት ሠርሆተ ሕዝብ ያደርጋሉ።

- ከቁርባን በኋላ የቀደሱት ካህናት የቆረቡት ምዕመናን እስከ በነጋው ድረስ እጅ እግርን መታጠብ፣ መስገድ፣ መንበርከክ፣ መራቆት፣ ምራቅ መትፋት፣ ሰውነትን ቆርጦ ደም ማውጣት፣ ጥፍር መቁረጥ፣ ራስ መላጨት፣ የሚያደክም ጉዞ መጓዝ፣ ከሰው ጋር መጨቃጨቅና፣ ወደ ውሽባ  ቤት መግባት፣ ከመጠን በላይ መብላት፣ መጠጣት፣ ሥጋዊ ፈቃድን መፈጸም ይህንና ይህን የመሳሰሉትን ማድረግ ክልክል ነው።

# ምስጢረ ቁርባን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት

## የምሥራቅ መለካውያን «ግሪክ፣ ሩሲያ፣ ቡልጋሪያ፣ ሩማኒያ፣ ቆጵሮስ...

- እነዚህ አብያተ ክርስቲያናት ልዩ የመሥዋዕት መሥሪያ የላቸውም፤ የሚያቀርቡት ምዕመናን ለበረከት ከሚያመጡት ኅብስትና ከተራ ዳቦ ቤት ገዝተው ነው። የቅዳሴው ጸሎት የትምህርቱ ክፍል ካለቀ በኋላ መስዋዕቱን በመንበር ላይ ያስቀምጡታል። ፍሬ ቅዳሴውን የሚጀምሩት ከዚያ በኋላ ነው።

- በቅዳሴም ጊዜ የሚነበቡ መጻሕፍት ከጳውሎስ መልእክትና ወንጌል ነው። ጳውሎስን የሚያነበው ዘማሪው ወይም መሪጌታቸው ነው። ከሌለም አስቀዳሾቹ ተራ ምዕመን ያነበዋል። ወንጌሉን ቄሱ ያነባል። ዲያቆን ካለም ዲያቆን ያነበዋል።

- ሥጋውና ደሙ ይለወጣል የሚሉት «በይረስዮ» ጊዜ ነው፤ ተለወጠ ካሉ በኋላ ለብ ያለ ውሀ አምጥተው በጽዋው ይበርዙበታል። የሚያቆርቡትም ሥጋውንም ደሙንም አንድ ላይ ከጽዋው ነው። የሚያቆርበውም ዲያቆን ካለ ዲያቆን፣ ከሌለም ቄስ ነው። በመጨረሻም ከቡራኬው ጋር ምዕመናን እየገዙ ያመጡትን ኅብስት ቆራርሰው ለአስቀዳሾቹ ምዕመናን ያድሏቸዋል። ከዚህ በኋላ ሠርሆተ ሕዝብ ይሆናል። የልዑካን ልክ የላቸውም ሃያ ሠላሳ ኹነውም ይቀድሳሉ። አንድ ቄስ ብቻውንም ይቀድሳል።

- የቅዳሴ ሰዓት ኹል ጊዜም ማለዳ ነው። በዓቢይ ጾም፣ ከእሑድና ቅዳሜ በቀር ቅዳሴ ክልክል ነው። እሑድ የቀደሱበትን በጽዋው አስንብተው ዐርብና ረቡዕ በሌሎችም አመች በኾኑ ዕለታት ጸሎተ ሠርክ አድርሰው ያቆርቡታል። ይኸም ብቻ ሳይኾን የጸሎተ ሐሙስ የቀደሱበትን እስከ ዓመት በመንበር ያስቀምጡታል አቁርቡኝ የሚል በድንገት ቢመጣ ለመጠባበቂያ ነው ይላሉ።

- ከኛ ጋር የሚመሳሰሉባቸው ኹለት ነገሮች ብቻ አሉ።
  - ሀ. በአንድ መንበር ኹለት ጊዜ አይቀድሱም፣
  - ለ. ኹል ጊዜ የሚቀድሱት በአኰቴት ነው።

# ምስጢረ ቁርባን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት …

## በምዕራቡ የላቲኖች

- ካቶሊኮች በምሥጢረ ቁርባን ከኛ ብዙ የተለዩ ናቸው:: መስዋዕት ብለው የሚያቀርቡ /በላቲን HOSTIA በእንግሊዘኛ HOST ይሉታል:: «መሥዋዕት» «VICTIM» ማለት ነው:: (ከሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምረው አሁን ባለው ሁኔታ ነው የሚቀድሱት:: Henry Chaduick, The early Church , London, 1969)
- በቅዳሴ ጊዜ የሚነበቡ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደ መለካውያን ናቸው:: አኹን ግን ባንዳንድ ቦታ ከብሉይ ኪዳንም ነቢያትን ሲያነቡ ይሰማሉ::
- ከሥጋውም ከደሙም የሚቀበል ቀዳሹ ብቻ ነው፤ ለምዕመናን ግን ሥጋውን ብቻ ያቀርቧቸዋል:: ይህም «ሥጋዬን የበላ ደሜንም የጠጣ የዘለዓለም ሕይወት አለው» ከሚለው አምላካዊ ቃል ጋር የማይስማማ ነው::
- ካቶሊኮች በምሥጢረ ቁርባን ከኛ የሚለዩት በዚህ ብቻ አይደለም ሌላም ብዙ አለ::
  ሀ. ከቁርስ በኋላ አንድ ሰዓት ቆይተው ይቆርባሉ ያቆርባሉ፣
  ለ. ባንድ መንበር ባንድ ቀን መላልሰው ይቀድሳሉ፣
  ሐ. መስገጃ ብለው በመንበሩ ላይ መስዋዕቱን ያስቀምጣሉ፣
  መ. የቅዳሴ ሰዓት ኹልጊዜም ማለዳ ነው::
  ሠ. አንድ ቄስ ብቻውን ይቀድሳል::
- በመጠኑ ከኛ የሚለዩት በእነዚህ ምክንያቶች ሲኾን ከዚህም ሌላ ቀኖናቸው በየጊዜው ስለሚለዋወጥ ብዙ ለውጥ በቤተ ክርስቲያናቸው ይታያል:: ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ የመንበሩን ገጽ ወደ ምዕራብ አዙረው ወደ ምዕራብ ይቀድሳሉ ይባላል::

# ምስጢረ ቁርባን በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት …

## በፕሮቴስንታቶች

- በእርግጥ ክህነትም ሥርዓትም ስለሌላቸው የሚሉትን ለማወቅ ያህል በመጠኑ እንመልከት:: መሥዋዕት ብለው የሚያቀርቡት የተለየ ዝግጅት የላቸውም:: ተራ ኅብስት ያቀርባሉ በኅብስቱ አምሳል ከኅብስቱ ጋር የክርስቶስ ሥጋ ይሰጣል ይላሉ:: ይህም ማለት ኅብስቱ ምሳሌ መሳሪያ (Symbol) ነው ማለት ነው:: (IN PANALIO/IN PANE በኅብስቱ ውስጥ CUM PANE ከኅብስቱ ጋር:: SUB PANE በኅብስቱ አምሳል) በአንቀጸ ተዋሕዶ መለካውያን የሚሉትን መሠረት በማድረግ የክርስቶስ አካል በኅብስቱ ያድርበታል ይላሉ::

- ይህ ትምህርታቸው ይህ ሥጋዬ፣ ይህ ደሜ ያለውን ያፈርሰዋል::

- እንደነሱ አባባል ኅብስቱ ምሳሌ ከኾነማ ቅዱስ ጳውሎስ «ይህን ኅብስት ሳይገባቸው የሚበሉት ዕዳ ይኾንባቸዋል» ያለው:: 1ኛ ቆሮ 11፥27:: የቅዱስ ጳውሎስ ትምህርት ምን ብለው ይተረጉሙታል?

- ይህ የነሱ አባባል ከቅዱሳት መጻሕፈትና ከቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ትምህርት የተለየ ነው:: የቤተ ክርስቲያን አባቶች ምሥጢረ ቁርባንን የማይመረመር ምሥጢር መኾኑን ያውቃሉ:: አርአያውና መልኩ ሳይለወጥ ልምላሜውና ጣዕሙ ሳይለየው ሥጋ መለኮት ደመ መለኮት ይኾናልናል:: በእርግጥ ሥጋውና ደሙ ሲለወጥ አይታይም:: ቅዱሳን ግን በተአምራት ሲለወጥ ያዩታል:: በምዕራብ ቤተ ክርስቲያን ያሉ ሊቃውንት የኅብስቱም የወይኑም ባህርይ ይለወጣል ብለው ይናገራሉ:: (Transubstantial)

- የምሥራቅ ቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት ግን በማይመረመር ግብር መለወጡን እንጅ የስንዴውንም ኾነ የወይኑ ጥንተ ባህርይ ለኹሉም ተለውጦ ይታያል ብለው አያስተምሩም::

# ማጠቃለያ ምክሮች

## ባል ወይም ሚስት ቅዱስ ቁርባን በመቀበል አለመግባባት ቢኖር ይኸን አድርጉ...

1. ሊያስተምር የሚችል ጥሩ የንስሐ አባት ያዙ።
2. የንስሐ አባት እንዲያስተምሩአችሁ ሁኔታዎችን አመቻቹላቸው።
3. ወደ ቤተክርስቲያን በመሄድ ትምህርት ተማሩ።
4. በንስሐ፣ በቁርባንና በትዳር ሕይወት ዙሪያ የተጻፉ መጻሕፍትን ማንበብ።
5. እግዚአብሔር ለቅዱስ ቁርባን ባልን/ሚስትን እንዲያነሳሳ (በስውር - ማንም ሳያውቅ) በጸሎት ጠይቁ።
6. መልካም ሕይወት ካላቸው ኦርቶዶክሳውያን ጋር ለመቀራረብ ሞክሩ።
7. ቁረብ/ቁረቢ እያሉ ከመወትወት የራስን ሕይወት አስተማሪ አድርጋችሁ አቅርቡ።
8. ከመኝታ በፊት መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብና መጸለይ።

# ይቆየን።

# ወስብሐት ለእግዚአብሔር።